# ህዝባዊው ቁጣ ሲዳሰስ .... (ክፍል አንድ)

አዜብ ጌታቸው

*October 10, 2016*




ሰላምና ጤና ለሁላችንም! ክብርና ምስጋና ሁሉን ለሚያስችለው ኃያሉ እግዚአብሄር ይሁን!

የመጨረሻውን ጽሁፌን ለንባብ ካበቃሁ ትንሽ ቆየሁ።በእረፍት ይሁን በመታከት ምክንያቱን እራሴም ባላውቀውም፤ መጫጫር አቁሜ ብዕሬን ሰቅዬ ቆይቻለሁ። የሚገርመው ደግሞ በነዚህ ግዚያቶች ውስጥ የህዝባችንን የ 25 ዓመታት የትግል ጉዞ አቅጣጫና መልክ የለወጡ በርካታ ነገሮች በተከታታይ መከሰታቸው ነው። አብዛኞቹ ክስተቶች ውድ የሆነውን የሰው ልጅ ህይወት የጠየቁ አሳዛኝ ክስተቶች ነበሩ። በዛው መጠን ከአሳዛኞቹ ተከታታይ ክስተቶች የተወለዱ፤ የህዝባዊ ትግሉን መልክ የለወጡ፤ ደርጃውን ከፍ ያደረጉ፤ አበረታች ነገሮችም እውን ሆነዋል። ጠየም ባለ አገላለጽ ሲነጋ ሲል ይጨልማል እንዲሉ አገዛዙ በማናለብኝነት በተከታታይ የፈጸማቸው አረመኔያዊ ተግባራት በራሳቸው የ 25 አመቱን የሰቆቃ ጉዞ ፍጻሜ ያፋጠኑ ተስፋ ሰጪ ክስተቶችን ወልደዋል ።

በመሆኑም በዛሬው ጽሁፌ የቆየሁበትን ግዜ ሂሳብ ለማወራረድ ስል አንዴ ወደፊት አንዴ ወደኋላ ስሯሯጥ ብታገኙኝ እንዳትታዘቡኝ ከወዲሁ አደራ እላለሁ።

**ለገዳዮች ሞትን ያስተማረ ጀግና!**

እንደ ቋያ እሳት ውስጥ ውስጡን ሲግም የቆየው የ 25 ዓመቱ ህዝባዊ ትግል ዛሬ የሚገኝበት የመጨረሻው መጀመሪያ ደረጃ እንዲደርስ መነሻ ምክንያት የሆነቺውና የታመቀውን የህዝብ ብሶት ያገነፈለቺው ኮለኔል ደመቀ በአጋዚ ታጣቂዎች ላይ የተኮሳት የመጀመሪያ ጥይት ነች ብል የተሳሳትኩ አይመስለኝም።

ኮለኔል ደመቀ ለ 25 አመታት በሰላም ገለው ሲገቡ የኖሩትን የአገዛዙ ታጣቂዎች በመይሳው ብሂል “እጅ መስጠት የለም!” ብሎ ሞትን አስተማራቸው። ጀግናው ኮለኔል የለኮሰው የድል ችቦ ዳር እስከ ዳር ተቀጣጠለ፤ የጎንደር ህዝብ ጀግናችንን አናስነካም ብሎ ዘብ ቆመ። የወልቃይት ህዝብ የማንነት ጥያቄ ወደ ጎንደር ህዝብ ጥያቄ ከፍ አለ።

**የአገዛዙን የዘር ፖለቲካ መርዝ ያመከነ ህዝባዊ ትዕይንተ ህዝብ!**

የጎንደር ህዝብ የአገዛዙን ፈቃድ ሳይጠብቅ ባደረገው ታሪካዊ የተቃውሞ ሰልፍ የኦሮሞው ደም የኔም ደም ነው ሲል የአገዛዙን የዘር ፖለቲካ መርዝ አመከነ። ጎጃምም ተከተለ። አዳማም የጎንደር ህዝብ ህመም ህመሜ ነው ሲል ምላሽ በመስጠት በወያኔ የከፋፍለህ ግዛ መቃብር ላይ የአበባ ጉንጉን አኖረ። ህዝባዊ ትግሉ በየአቅጣጫው ተቀጣጠለ…አገዛዙም…በርካታ ንጹሃንን ገደለ።

**ሸገር ሲጠበቅ ሪዮ የፈነዳው ተቃውሞ፤**

ጎንደር የተለኮሰው የተቃውሞ ችቦ ፤ ወደ ጎጃም ተሻግሮ ፤ በአዳማና አካባቢው ሰነባብቶ፤ ሸገር እንደሚገባ ሲጠበቅ በድንገት አሃጉር ተሻግሮ በላቲን አሜሪካ ሪዮ ዲጄኔሮ ላይ ተከሰተ። ወቅቱ የፈጠረው ሌላው ጀግና ፈይሳ ሌሊሳ በቢሊዮን ለሚቆጠረው የአለማችን ህዝብ የወያኔን ነውርና ገበና አጋለጠ። ህዝባዊ ትግሉ ዳግም ላይዳፈን ተቀጣጠለ። ወያኔ አሁንም መግደሉን ቀጠለ።

**ሰከን በሉ እንጂ…!**

ሰከን በሉ ! የተሰኘው የይሁኔ በላይ ዘፈን ስሜትን ሰርስሮ ለመግባት አፍታ አይወስድበትም። በግጥሞቹ የሚተላለፉት አሳዛኝ፤ ገሳጭ፤ አሳሳቢና ተማጻኝ መልዕክቶች ከፊል የሙሾ ድምጸት ካለው ዜማ ጋር ፍጹም ሆነው የተዋሃዱበት ድንቅ! ዘፈን ነው።

ሰከን በሉን እያደመጡ የሚያነቡ ብዙዎችን አይቻለሁ። እኔም ብሆን ዘፈኑ ተከፍቶ እስኪጠናቀቅ ድረስ በማላውቀው የቁጭትና የሃዘን ስሜት ውስጥ ተዘፍቆ ራሴን አገኘዋለሁ ። ለምን እንደሆን ባላውቅም አንዳንድ ዘፈኖች ከአቀንቃኛቸው ድምጽ ጋር ያላቸው ውህደት በሌላ ዘፋኝ ሊዘፈኑ አይችሉም እስከማለት ያደርሱኛል። የይሁኔ በላይ “ሰከን በሉ” ንም እንደሱ ማንም ሊዘፍነው የሚችል አይመስለኝም።(ቢያንስ ለኔ)

በዚህ አጋጣሚም ይህን ታሪካዊ! ወቅታዊና ስሜት ሰርሳሪ! ዘፈን ለተጫወተልን አርቲስት ይሁኔ በላይና በሙዚቃው ስራ ላይ ሙያዊ ተሳትፎ ላደረጋችሁ ወገኖች ሁሉ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ። የተገፋው ህዝባችሁ ድምጽ ሆናችኋልና።

በነገራችን ላይ ሰከን በሉ የወጣው በአዲስ አመት ዋዜማ ነበርና የአዲሱን አመት አቀባበል መልክ የቀየረ ዘፈን ነበር።የሃዘን ሳምንትን ያወጀ ዘፈን።

**አርቲስቱ ህዝብን ያከበረበት የጥቁሩ ሳምንት አዲስ አመት፤**

የ 2009 አዲስ አመት የተከበረው በኢትዮጵያ የአዲስ አመት አከባበር ታሪክ ሆኖ በማያውቅ (ቢያንስ ቢያንስ ለአቅመ-ግንዝቤ ደርሼ እስከማውቀው ድረስ) ብሄራዊ የሃዘን ስሜት ነበር። ከሊቅ እስከ ደቂቅ የተባበረበት፤ በተለይ በዓሉን አድማቂ የሆኑን አርቲስቶች አዋጅ ሳይነገር እንቢልታ ሳይመታ በራሳቸው አነሳሽነት ኮንሰርታቸውን ሰርዘው ህዝባዊ ወገንተኝነታቸውን ያሳዩበት፤ ልዩ የታሪክ ምዕራፍ ነበር። ሃዘንተኞች ነን ዝፈኑ አትበሉን! በወገን ደምና ሬሳ ላይ ዳንኪራ አንጨፍርም አሉ! አርቲስቶቻችን። ቁጥራቸው ወደፊት ሂሳብ ሲወራረድ በግልጽ የሚታወቅ ቢሆንም የወገናቸውን ደም ተራምደው የጨፈሩ ጥቂቶች አልጠፉም። ቁጥራቸው ግን እዚህ ግባ የሚባል አይመስለኝም።

ለማንኛውም ግን አመታዊ ወፍራም ገቢያቸውን በአፍንጫዬ ይውጣ ብለው ከወገናቸው ጋር በሃዘን ተኮራምተው ማሳለፍን ለመረጡት አርቲስቶቻችን ክብር ለነሱ ይሁን ።አዲሱን አመት ከፊል ሃዘንና ከፊል ተስፋ በሰነቀ ድብልቅልቅ ስሜት ነበር የተቀበል ነው። ሃዘኑ በአረመኔዎች ጥይት ህይወታቸውን ላጡ ንጹሃን ወገኖቻችን ሲሆን ተስፋው ደግሞ ከነቀርሳው የህውሃት ወያኔ አገዛዝ መፈወሻችን መቅረቡን ማመላከቱ ነው።

**ብሄራዊ ሠርግ! ሰብአዊ ትዳር!**

ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት የተሰቀለውን ብዕሬን አንስቼ ዳግም እንዲቧጥጥ እንዳስገደድኩት እኔንም ያስገደደኝ የሙሽሪት ሜሮን ሰባዊነትንና አገር ወዳድነትን አዳብሎ ያንጸባረቀው ቃላት ሊገልጸው የማይችለው ገድሏ ነው። የሜሮን ተግባር ለኔ በጦር ሜዳ ከሚገኝ የጀግንነት ገድል የሚያንስ አይደለም።(አላጋነንኩም! አላዳላሁም)።

ከላይ ጠቆም እንዳደረኩት የይሁኔ በላይ "ሰከን በሉ!" ልዩ የሆነ ስሜት ሰቃፊ ምህታታዊ ኃይል አለው። ሙሽሪት ሜሮንንም ለዚህ ታሪካዊ ተግባር ያነሳሳት ይኸው ምህታታዊ ሃይል ይመስለኛል።

በነገራችን ላይ ከጥቂት ግዜ በፊት ሜሮን ጌትነት "አትሂድ" በሚል ርዕስ የጻፈቺውን ግጥም አስመልክቶ አድናቆቴን መግለጼን አስታውሳለሁ። ዛሬ ደግሞ ሌላዋ ሜሮን እንዲሁ ብዕሬን እንዳነሳ ምክንያት የሆነ ተግባር የመፈጸሟ አጋጣሚ ሳያስገርመኝ አልቀረም ። ይሄ ነገር ከስሙ ይሆን እንዴ? ያስባለኝ ግን በሃገር ጉዳይ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ የሚታወቁትን በስሜን አሜሪካ የሚገኙ ሜሮኖችን ሳስታውስ ነው ሜሮን አሃዱና አኃናፍር።

ወደ ሙሽራዋ ሜሮን ልመለስ፦ሜሮን "ሰከን በሉ"!ን ከይሁኔ እኩል እየተጫወተች ግጥሞቹ የያዙትን መልዕክት በእንቅስቃሴዎቿ የምትገልጽበት መንገድ ደግሞ ሌላው ያስደነቀኝ ብቃቷ ነው።የአንበሳን ጥንካሬ- በክርኗ፤ የመሳሪያውን ቃታ- በሌባ ጣቷ ፤ ሰክነትን – በጣቶቿ ስብቀት እያሳየች ስትንቀሳቀስ ልዩ ነች። ከውስጥ እየፈነቀለ የሚወጣው ስሜቷ ከሙዚቃው ጋር አንድ አካል አንድ አምሳል ሆነው ተዋህደዋል። እንደኔ እምነት ይሁኔ በላይ ከዚህ በላይ ምንም አፊሻል ክሊፕ የሚያስፈልገው አይመስለኝምና ይህንኑ ቢያጸድቀው እመክረዋለሁ። (ምክር ነው)

ከዚህ ሁሉ በላይ ግን የሜሮንን ተግባር ክቡርና ድንቅ ያደረገው "…..ከሞት አንድ ነው" በሚባለው በሠርጓ እለት የወገኖቿን መከራ፤ ሞትና፤ስቃይ ለመዘከር መወሰኗ ነው። ይህን ውሳኔዋን ምናልባት ለወዳጅ ዘመዶቿ ቀደም ብላ አማክራ ቢሆን "እረ ተይ!" በዓለምሽ ቀን የምን ሃዘን ነው? ሊሏት ይችሉ እንደነበር እገምታለሁ። እሷም ይህንኑ ፈርታ ይመስለኛል ሃሳቧን ለእጮኛዋ (አሁን ባለቤቷ) ብቻ ያማከረቺው፡፡ ባለቤቷም ሰብአዊ ስሜቷን አድንቆ ሃሳቧን መደገፉ የሚያስመሰግነው ነው። ትዳራቸውን ሰብአዊ ትዳር፤ሰርጉን **ብሔራዊ ሠርግ** ያልኩትም ለዚህ ነው።

እናም እህቴ ሜሮን ሆይ! ይህን በማድረግሽ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ሲያከብርሽ ይኖራል። ሰርግሽም በኢትዮጵያ የሰርግ ታሪክ ልዩ ምዕራፍ ይዞ ይዘከራል። ልጆችሽም በእናታቸው ገድል ይኮሩ ዘንድ ማድረግ ችለሻልና! እንኳን ደስ አለሽ! ዘርሽም ይባረክ! ትዳርሽም የሰመረ ይሁን!እላለሁ። ለክርስትና እንመጣልን ገና ብለናል ! የምንመጣው ግን ሸገር እንጂ አሜሪካ አይደለም።

**የፕሮፌሰር መስፍን የመፍትሄ ሃሳብ (የትግራይ ህዝብ ሆይ ለራስህ ስትል ጣፍጥ)**

ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት የዛሬው ጽሁፌ ላለፉት ጥቂት ወራት የተከሰቱ ጉልህና አነጋጋሪ ነበሩ ያልኳቸውን ክስተቶች በወፈ በረር የሚቃኝ ነው። እናም እውቁ የሰባዊ መብት ተሟጋችና አንጋፋው ምሁር ፐ/ር መስፍን ወልደማሪያም “የወያኔ አገዛዝና የኢትዮጵያ ወደፊት” በሚል ርዕስ ለንባብ ያቀረቡት በ11 ገጾች የተካተተው ጽሁፍ ከጉልህ ክስተቶች አንዱ ነበርና በወፍ በረር ምልከታዬ ላካትተው ፈለኩ።

የፐ/ር መስፍን ወልደማሪያምን ጽሁፍ እንዳነበብኩ ወዲያው በአይምሮዬ ያቃጨለው ከ 25 ዓመታት በፊት በሳቸው አነሳሽነት (ሌሎችም ምሁራን በሃሳብ የተጋሩት ይመስለኛል) ለኮ/ል መንግስቱ ኃይለማሪያም ያቀረቡት የስልጣን ልቀቅ ደብዳቤ ነው። ታሪክ በሚያስገርም መልክ ራሱን ሲደግም ታየኝና እኝህ ሰው መንግስት ሲያቅተው የሚታያቸው ነገር አለና ወያኔ ለ 12 አምስት ጉዳይ ላይ እንደሚገኝ አንድ ማረጋገጫ ነው አልኩ። ደስም አለኝ። ከወገቤ ሸብረክ ብዬ መምህር ሆዬ! እድሜ ይስጥልን እንኳን በህይወት ቆይተው ይህንንም መንግስት “ይብቃህ ውረድ!” ለማለት በቁልን ብያለሁ።

ወደ ፐ/ር ጽሁፍ ይዘት ስመጣ፦ በፐ/ር ጽሁፉ የተገለጹት አብዛኞቹ ሃሳቦች የሚያከራክሩ አይደሉም።

ፐ/ር በጽሁፋቸው **1ኛ)** ኢትዮጵያ እንደ ሃገር የምትገኝበትን አሳሳቢ ሁኔታ አመላክተዋል።

2ኛ) የትግራይ ህዝብ የአገዛዙ (የወያኔ) ዱዳ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ ለምርጫ አስቸጋሪ የሆነ(ላም እሳት ወለደች...) አይነት የታሪክ ምዕራፍ ላይ እንደሚገኝ አብራርተዋል። የትግራይ ህዝብ ሁለት ምርጫዎች ከፊቱ ተደግነዋል **1ኛው)** ከወያኔ ጎን መቆም **2ኛው)** ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር መቆም እንደሆነ ጠቁመው፤ እንደ ምክርም ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር እንዲቆም አሳስበዋል። የትግራይ ህዝብ ሆይ! ለራስ ብለህ ጣፍጥ አልያ .... አይነት ድምጸት ያለውን ማሳሳቢያና ምክርን አዋህደው አቅርበዋል።

3ኛ) አገዛዙ (ወያኔ)እያዋከበው ከሚገኘው ህዝባዊ አመጽ ሊወጣ ከማይችልበት ደረጃ መድረሱን አመላክተው ነገር ግን የአገዛዙ አካላት መልካም ፍቃድ ከታከለበት (መልካም ፈቃድ ብሎ ነገር ባያውቁም አሁን ግን ከየትም ያምጡት ብለው) ስልጣን በሰላም ለቀው ለራሳቸውም ለትግራይ ህዝብም ለኢትዮጵያም የሚበጅ ነገር ማድረግ እንደሚችሉ የደቡብ አፍሪካውን ዴክለር ዋቢ አድርገው አስረድተዋል። አስከትለውም የአገዛዙ መልካም ፈቃድ ከተገኘ በቀጣይ ሊደረጉ ይገባል ያሏቸውን የመፍትሄ ሃሳብ ዝርዝሮች (ለውይይት) አቅርበዋል።

በፐ/ር ለቀረበው የመፍትሄ ሃሳብ ትልቁ እንቅፋትና ተግባራዊነቱን የህልም ያህል የማይጨበጥ የሚያስመስለው መልካም ፈቃድ ብሎ ነገር በማያውቁት ባለስልጣናት “መልካም ፈቃድ” ላይ የተመሰረተ መሆኑ ነው። ፐ/ር ይህ መሆኑ የጠፋቸው አይመስለኝም። “መልካም ፈቃዱን” ከየትም ያምጡት ያሉትም ለዚህ ነው፡፤ ችግሩ መልካም ፈቃዱን ከየት ያመጡታል ?

ለረዥም ግዜ የፐ/ር መስፍን ጽሁፍ ሳነብ ቆይቻለሁ! ፐ/ር ሁሌም ቢሆን እገሌን ይከፋዋል እገሌን ያስደስተዋል በሚል ይሉኝታ የሚያምኑበትን ነገር ከመግለጽ ወደ ኋላ እንደማይሉ ሁሉ የማይምኑበትንም ነገር ኤክስ ለመስጠት አይፈሩም።

በዚህ ጽሁፋቸው ላይ ግን ሊሆን እንደማይችል ነፍሳቸው እያወቀች ምናልባት... እንዲያው ምናልባት... በሚል ቀጭን ተስፋ ላይ የተንጠለጠለ የመፍትሄ ሃሳብ መሰንዘራቸውን አስተውያለሁ። ይህ ደግሞ ፐ/ር በርግጥም በጣም...! በጣም..! መጨነቃቸውን እንድገነዘብ አድርጎኛል ። ፐ/ር ከ ቪ.ኦ.ኤ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስም “ተስፋ ቆርጫለሁ” ማለታቸው ይህንኑ ጭንቀታቸውን

የሚያሳይ ሆኖ ተስምቶኛል። ፐ/ር በዚህ ጽሁፋቸው ዙሪያ በተደረገላቸው አንድ የፓልቶክ ቃለ-መጠይቅ ላይ፤ አዲስ መጪው ሂያጁን እየተበቀለ የሚቀጥልበትን መጥፎ ልምድ(አዙሪት) አንድ ቦታ እናቁመው! ቂምን አርግዘን ለበቀል ከመንደርደር ወጣ ብለን ስለዘላቂ ሰላም እናስብ የሚል ይዘት ያለው አባታዊ ምክርም ሲያስተላልፉ አድምጫለሁ፡፡

ያም ሆነ ይህ አገዛዙ ምክራቸውን ተቀበለም አልተቀበለ! ፐ/ር በተለይ የትግራይ ህዝብ በነገዋ ኢትዮጵያ ህልውና ላይ አዎንታዊ አልያም አሉታዊ ሚና የመጫወት ምርጫው ከፊቱ መደቀኑን አበክረው ያሳሰቡበት ክፍል ወቅታዊና ታሪካዊ ማሳሰቢያ ነው እላለሁ። ውድ ፐ/ር እድሜ ሰጥቶዎት የኢትዮጵያን ትንሣኤ ለማየት ያብቃዎት እያልኩ ወደ ሌላው ምልከታዬ ልዝለል።

**አቶ ያሬድ ጥበቡ ሆይ! ለአቶ አዲሱ ለገሰ የሽግግር መንግስት ወንበር ሳይሆን የመቃብር ቦታ አፈላልግለት!**

ሌላው የሰሞኑ ጉልህ ክስተት በይሆንም በዛሬው ምልከታዬ በጥቂቱም ቢሆን ልነካካው የወደድኩት አቶ ያሬድ ጥበቡ "ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ ወደ ዋሽንግተን ይመለስ" በሚል ርዕስ ለንባብ ያቀረበውን ጽሁፍ ነው።

አቶ ያሬድ ዶ/ር ብርሃኑ ወደ ዋሽንግተን እንዲመለሱ ሲል ያቀረበውን ሃሳብ በምክንያት ሲያስረዳ፡ ከ 40 ዓመት በላይ ወደ ኋላ ተጉዞ ብርሃነ መስቀል ረዳ በኤርትራ በርሃ እያለ ድንገት በተቀሰቀሰው የየካቲት 66 አብዮት ሊጫወት የሚችለውን የመሪነት ሚና ሳይጫወት መቅረቱን አስታውሶ ፤ ይህ የብርሃነ መስቀል መጥፎ አጋጣሚ ዛሬ በኤርትራ ምድር በሚገኙት ዶክተር ብርሃኑም ላይ እንዳይደገምና ዶክተሩ እየተቀጣጠለ ባለው ህዝባዊ አመጽ ሊጫወቱ የሚችሉትን ጉልህ ሚና ሳይጫወቱ እንዳይቀሩ ስጋት እንዳደረበት ያስረዳል።

አቶ ያሬድ ምጸት በሚመስል መልክ ታሪክ እራሱን እንዳይደግም በሚል ያቀረባቸው ሁለት የታሪክ አጋጣሚዎች የሚመሳሰሉት ሁለቱም የትግል መሪዎች ህዝባዊ እንቅስቃሴ በተቀጣጠለበት ወቅት ኤርትራ ምድር መገኘታቸው ነው። ይህ በርግጥም ተመሳሳይ አጋጥሚ ነው።ነገር ግን የብርሃነ መስቀል እጣ ፈንታ የዶክተር ብርሃኑም ሊሆን ይችላል የሚለው ስጋቱ ግን በሁለቱ ክስተቶች መካከል ያለውን የ 40 ዓመታት ልዩነት ያገናዘበ አይመስለኝም።

ብርሃነ መስቀል በበቅሎ ጀርባም ይሁን በእግር ተጉዞ አሲንባ ለመድረስ የፈጀበትን ግዜ ያህል ዛሬ ዶክተር ብርሃኑ የትግሉ ማዕከል ወደ ሚሆነው የትኛውም ስፍራ ለመድረስ ይፈጅባቸዋል ተብሎ አይታሰብምና ነው። ዋናው ቁምነገር ደግሞ ከትግሉ ወላፈን በምን ያህል ርቀት ላይ እንደሚገኙ ከማናችንም በላይ ዶ/ሩ የሚያውቁት ይመስለኛልና ይሄ ብዙ የሚያሳስብ አይመስለኝም። ያም ሆነ ይህ አቶ ያሬድ ይበጃል ያለውን መምከሩ ክፋት የለውም፡፡ ዶክተሩ በህዝባዊ እንቅስቃሴው ውስጥ ሊጫወቱ የሚችሉትን ጉልህ ሚና ያስረዳበትን ክፍል መሉ ለሙሉ እጋራዋለሁ።

ይህች አጭር ምልከታ እንድሰነዝር ምክንያት የሆነኝ የአቶ ያሬድ ሃሳብ ግን የስካሁኑ አይደለም። "ወጣ ወጣና እንደሸንበቆ ..... እንደ .... " ያሰኘኝ፡- የወቅቱን ህዝባዊ እንቅስቃሴ የሚመራ፤ ከሁሉም የፖለቲካና የብሄር ድርጅቶች የተውጣጣ አንድ ቡድን እንዲቋቋም ምክር የሰጠበት ክፍል ነው።

አቶ ያሬድ ይህንኑ የአመራር ቡድን ሲያዋቅር፡- ከግንቦት ሰባት እነ ዶ/ር በርሃኑ ፤ ከኦሮሞ አክቲቪስቶች እነ ጅዋርንና እነ በቀለ ገርባ …… አለ አለና በአሁኑ ወቅት የአማራውን ብሄር በመወከል የሚንቀሳቀሱት ወጣቶች ብዙም ስላልበሰሉ (ልጆች ስለሆኑ) አዲሱ ለገሰን ማካተቱ ይጠቅማል ብሎ እርፍ።

ይህን ካነበብኩ በኋላ አቶ ያሬድ የቆመበትን ቦታ ማወቅ አቃተኝ። ስለ ብአዴን ያለው አመለካከት ከጓደኝነት ስሜት ያልዘለለ ሆነብኝ። ወጣቶቹን አልበሰሉም ለማለት የደፈረ ሰው እራሱ….? ስል ጠየቅኩ። ደግሞ ወዲያው፤ አባባሉ ምናልባት ወያኔን በመከፋፈልና በማስደንገጥ ረገድ ጥቂትም የስትራተጂ ጠቀሜታ ይኖራት ይሆን ብዬ አሰብኩ ። በምንም ይሁን በምን ሊዋጥልኝ አልቻለም።ደግሞስ በምን መለኪያ ነው የቮሊቦል መምህሩ "አዲሱ ለገሰ" አሁን ለአማራ ሙብት መከበር ከሚንቀሳቀሱት የተማሩ ወጣቶች የተሻለ የሚሆነው? ራሴን ጠየቅኩ በመጨረሻም ለአቶ ያሬድ አልኩ፡-

አቶ ያሬድ ሆይ! አዲሱ ለገሰ በነገዋ ኢትዮጵያ ላይ ሚና እንዲኖረው ወንበር ከምታፈላልግለት ይልቅ ከወያኔ መቃብር ግርጌ የመቃብር ቦታ ብትይዝለት ይሻላል። በመቃብሩ ላይ ቆሞ አማራን ያልጠቀመው ሞቶም የማይጎዳው የቮሊቦል መምህሩ አዲሱ ለገሰ ይህ ነበር የሚል የግንባር ጽሁፍ እንዲያርፍ እኔም ምክሬን ላንተ እለግስሃለሁ። (ይህን ስል ህዝባዊ ትግሉን በህቡ የሚያግዙ የብአዴን አባላት ሊኖሩ አይችሉም ከሚል እሳቤ እንዳልሆነ ይታወቅልኝ! አዲሱ ለገሰ ግን ከብአዴን ለህወሃት ይቀርባል)

ለዛሬው በዚሁ ላብቃ በቅርቡ በዚህ ጽሁፍ ያልተካተቱ ሰሞነኛ ክስተቶችን በምዳሥበትና ከዚህ ወዴት? በሚለው ጥያቄ ላይ የታየኝ በምገልጽበት (እንደ ሁለተኛ ክፍል) ሊወሰድ በሚችል ሌላ ጽሁፍ እስክንገናኝ ሰላም ሁኑልኝ!

የኢትዮጵያ ትንሣኤ ቅርብ ነው።

አዜብ ጌታቸው

azebgeta@gmail.com